# የትራንስፎርሜሽን እቅዱ ስኬት!!

ተክሉ 03/19/14

የአምስት ዓመቱ መሪ የሀገሪቱ ብሔራዊ የትራንስፎርሜሽን እቅድ ሲወጣና በተለያዩ መድረኮች ለውይይት ሲቀርብ ተቃዋሚውም ተጋብዞ  አስተያየቱን እንዲሰጥ ሲደረግ እጅግ የተጋነነና ሊሳካ የማይችል የሀገሪቱን አቅምና እድገት ያላገናዘበ ኢሕአዴግ የፓለቲካ ትርፍ ለማግኘት በአማላይነት ያቀረበው ነው ሲሉ ተችተውታል፣ ነቅፈውታል፣ አብጠልጥለውታል፡፡ በየግሉ ጋዜጣና መጽሄትም ተሳልቀውበታል፡፡ የኢሕአዴግ ቅዠትና ወደ መሬት የማይወርድ ህልም ነው ብለውታል፡፡ የሀገር ውስጡ ተቃዋሚ ሁሉንም ነገር ከጥላቻ ስሜት ተነስቶ ስለሚያይ ክፉኛም አጣጥለውታል፡፡

የትራንስፎርሜሽን እቅዱን የደገፉና ያደነቁ ይኼ በዚህ ቢሆን የተሻለ ውጤት ያመጣል ያሉ ህዝባዊ  እና አገራዊ ኃላፊነት የሚሰማቸው፣ የሀገሪቱ መሻሻልና ጥሩ እድገት የእኛም ነው ብለው የሚያምኑም በጎ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ የውጪ ለጋሾችና የበለጸጉ አገራት ተወካዮች ኢትዮጵያ ይህን ልታሳካ አትችልም፣ አቅም የላትም፣ እንኳን በኢትዮጵያ አቅም በሌሎችም ደረጃ የትራንስፎርሜሽን እቅዱ የተጋነነና ለማሳካት የማይቻል ነው ብለውታል፡፡

የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊና ፓርቲያቸው ኢሕአዴግ ለኢትዮጵያ ታላቅ እድገትን ተመኝተው ይህንን ሲያቅዱ የተማመኑበት ትልቁ ተዐምር ሰሪ ኃይልና የስኬቱ ሞተር እና ተዋናይ የሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ ከዳር ያደርሰዋል ብለው ነው፡፡ ህዝብ ታላቅ ኃይልና ጉልበት ነው፡፡

የህዝብ እውቀትና ጉልበት በገንዘብ የማይለካ የማይነጥፍ እያደር እየጠጠረ  የሚሄድ ግዙፍ ካፒታል ነው፡፡ የማይነጥፍ የኢንቨስትመት ኃይል ነው፡፡ ጋራውን ወደ ሜዳ ለውጦ፣ ገደሉን ደልድሎ፣ የእርሻ ማሣው ያጋጠመውን መሸርሸር ገድቦ፣ ተረተሩን አልምቶ፣ ወደ ድህነት የሚወስደውን በረሃ ወደ ገነት የሚቀይር መተኪያ የሌለው የታመቀ ኃይል ነው

ያለው፡፡ ህዝብ ብልህትና ጥበብን ስለሚያስተምር አዳዲስ ዘዴንም ስለሚያፈልቅ የዓለም የመለወጥ ኃይልና ስኬት ሚስጥሩም እሱው ነው፡፡

እሥራኤል የበረሃውን አሸዋና መሬት እውቀትን ተጠቅማ በመለወጥ በህዝቧ አማካይነት የተመቸና የተደላደለ የበሀረ ገነት ህይወት በመፍጠር በዓለም ምርጥ የተባለውን የጃፋ ብርቱካን ለማምረት በቅታለች፡፡ ጃፓን፣ ቻይና፣ ደቡብ ኮሪያ ከዛሬ 50 ዓመት በፊት በዓለማችን ድሃ የሚባሉ ሀገሮች ነበሩ፡፡ ዛሬ የደረሱበት የኢኮኖሚ ምጠቀት እና የላቀ የቴክኖሎጂ ብቃት ጣሪያ ወሣኝ በሆነው የህዝብ ኃይልና ትግል የደረሱበት ነው፡፡ ከድህነት ተነስተው እውቀትንና የህዝብ ወሣኝ ኃይልን፣ የሥራ ዲሲፕሊን፣ ጽናትና ትጋትን፣ አይበገሬነትን፣ እልህን ሰንቀው ሌት ተቀን በመሥራታቸው ነው ዛሬ ላሉበት ደረጃ የበቁት፡፡

ከዛሬ 50 ዓመት በፊት የዓለም የመጨረሻዎቹ ድኃ የነበሩ አገሮች ዛሬ የዓለም ኢኮኖሚ መሪዎች ሰንጠረዥ ውስጥ ለመግባት በቅተዋል፡፡ የኤሺያ ታይገር ተብለው የሚጠሩት በኢኮኖሚ እድገት ተዓምር ማስመዝገብ የቻሉት አገራት ከድህነት የወጡት የትራንስፎርሜሽን እቅድና ስትራቴጂ የእድገት አቅጣጫ ቀይሰው ወሣኝ በሆነ ዲሲፕሊን ህዝቡን በማሰለፋቸው ነው፡፡ የትናንትዋ ብራዚል፣ ህንድና ቻይና የኢኮኖሚ ስኬታቸው እድገትና ሚስጥሩ በህዝቡ ትጋትና ቁርጠኛ ተሳትፎ፣ በጠንካራ አመራር ቁጥጥር እና ግምገማ እንዲሁም በተግባራዊነት ላይ የተመሠረተ ሥራ ለመከወን በመብቃታቸው ነው፡፡

በኢትዮጵያም የትራንስፎርሜሽን እቅዱን ለማሳካት ወሣኙ ኃይል ህዝብ ነው፡፡ ኢህአዴግ የአምስት ዓመቱን መሪ የኢኮኖሚ የትራንስፎርሜሽን እቅድ ሲያወጣ በርካታ የዓለማችን አገራት ከድህነት በአጭር ጊዜ ለመውጣት ያካሄዱትን ትግልና የስኬት ሚስጥሮችን በሚገባ ፈትሿል፡፡ ተቃውሞ እንደሚያጋጥመው ጠንቅቆ ያውቅም ነበር፡፡

ከመሥራትና ተግባራዊ ለውጥ ከማምጣት ይልቅ በጨለምተኛ አስተሳሰብና በማያባራ ጥላቻ የተዘፈቀው ኃይል የሚመጣውና የሚገኘው ለውጥ የአገሩ መሆኑን እንኳን ለማስተዋል አልታደለም፡፡ የኒዮ ሊበራል ኃይሉ ኢኮኖሚስቶች ይህን የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን እቅድ የገዘፈና የተጋነነ ነው ከማለትም አልፈው ከድህነት የመነጨ

አጉል ተስፋና ቅዥት አድርገው እንደወሰዱትም ይታወቃል፡፡ ይህ እልህና ቁርጠኝነት ነው የስኬቱን በር የከፈተው፡፡

ሀገራዊ የሰው ኃይልና ጉልበት፣ እውቀትና የተፈጥሮ ሀብት፣ በእጅ የሚገኝን የራስ ካፒታል በአግባቡ እና በቁጠባ ይዞ በመጠቀም፣ መሬቶችን በዘመናዊ ዘዴ በማረስና ተረፈ ምርት በማምጣት፣ የኖረን ወራጅ ውኃ ጠልፎ መስኖ በመጠቀም ልማትን በማካሄድ፣ በታላላቅ ወንዞች ላይ ግደብ ሰርቶ የኃይል ማመንጫ መገንባትና ለአገሪቱ ማዳረስ ወደ ውጭም መሸጥ፣ ጂኦተርማል የንፋስ ኃይልን ለኤሌክትሪክ ኃይል ምንጭነት መጠቀምና ሌሎችም ታላቅ ተዐምራዊ የኢኮኖሚ ለውጥን አስገኝተዋል፡፡

ኢሕአዴግ አይሳካም ቅዥት ነው የተባለውን የአምስት ዓመት የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን እቅድ በሦስት ዓመታት ውስጥ ወሣኝ የሆነውን የህዝብ ኃይል በመጠቀም ወደ ታላቅ ስኬት ምዕራፍ አሸጋግሮታል፡፡ ይህም የጨለማና እኩይ አስተሳሰብ ያላቸውን የውስጥ ተቃዋሚና የውጩን ጽንፈኛ ተቃዋሚ ኃይል አሳፍሮታል፣ አሸማቆታል፡፡

ህዝብ ለውጡንና እድገቱን በዓይኑ አይቶታል፣ ጨብጦታል፣ መስክሯል፡፡ ምዕራባዊያን መንግሥታትም ሆኑ ለጋሽ ዓለም ዓቀፍ የኢኮኖሚ ተቋማት ኢትዮጵያ ከድህነት ለመውጣት የተያያዘችውን ትግልና ትቅንቅ አይተውና ፈትሸው በአፍሪካ ሁለተኛ በዓለም አሥረኛ ደረጃ የምትገኝ በፈጣን የኢኮኖሚ እድገትና ግስጋሴ ላይ ያለች አገር መሆኗን ደግመው ደጋግመው መስክረዋል፡፡

በአንድ ሀገር ውስጥ ለኢኮኖሚ እድገት ወሣኝ ሚና የሚጫወተው በሸቀጥ አቅርቦትና ሥርጭት እንዲሁም በንግድ በኩል ያለ ሥራ የሚቀላጠፈው ሰፊ መሠረተ ልማት ሲዘረጋ በመሆኑ በመዲናዋ አዲስ አበባም ሆነ በመላው አገሪቱ ዘመናዊና ደረጃቸውን የጠበቁ የአስፋልት መንገድ ሥራዎች በስፋት ተሰርቶ ተጠናቋል፡፡

ቀድሞ መንገድ በሌለባቸው ሥፍራዎች ፒስታና አዳዲስ አገናኝ መንገድ ተዘርግቷል፡፡ በርካታ የገጠርና የከተማ ቦታዎችን የሚያገናኙ መንገዶች ተስፋፍተዋል፡፡ ብዛት ያላቸው የጤና ጣቢያዎች፣ ክሊኒኮች፣ ሆስፒታሎች፣ በየክልሉ ተሰርተዋል፡፡ የጤና፣ ትምህርትና

የወሊድ ምክር አገልግሎት በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም በየክልሉ በመዘርጋቱ የህፃናትና የእናቶችን ሞት  መቀነስ ተችሏል፡፡

በአገሪቱ በብዙ ሺህ የሚቆጠር የጤና ባለሙያ ከመንግሥትና ከግል ኮሌጆች ተመርቆ በመውጣት በተለያዩ መስኮች ተሰማርቶ በሁሉም ክልሎች አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡

አንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲሁም ዩኒቨርሲቲዎች በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ መልኩ በሁሉም የአገሪቱ ክልሎች ተስፋፍተው የኢትዮጵያን ወጣቶችን በእውቀት ለማብቃት እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ ቀድሞ በኢትዮጵያ ሦስትና አራት ብቻ የነበሩት ዩኒቨርሲቲዎች ዛሬ ከ37 በላይ ደርሰዋል፡፡ የመከላከያ ዩኒቨርሲቲዎችና የምርምር ማዕከሎችም ከዚህ በፊት ባልነበሩ መልኩ ተገንብተዋል፡፡

የመከላከያ ኢንጂነሪንግ ለአገሪቱ ዘመናዊ የከባድ ኢንዱስትሪ ግንባታ የሚያስፈልጉትን የተለያዩ ብረታ ብረቶችንና መለዋወጫዎችን የውጭ ምንዛሪን በማስቀረት ራሱን ችሎ ያመርታል፡፡ የተለያዩ አምራች ኢንዱስትሪዎችም አሉት፡፡ የተለያዩ ከባድና ቀላል መኪናዎችን በአገር ውስጥ ይገጣጥማል፤ ያመርታል፡፡ ቀላል እና ከባድ የጦር መሣሪያዎችን ጥይቶቻቸውን በአገር ውስጥ በራስ ባለሞያ ማምረት ተችሏል፡፡

በአስደናቂ ሁኔታ በኢትዮጵያውያን የመከላከያ መሀንዲሶች ሰው አልባ የሆነች ለቅኝት ተግባር የምትውል እና በከፍተኛ ርቀት የምትበር እይታ የማትገባ አነስተኛ ድሮን አይሮፕላንና ሄሊኮፕተርም ተሰርቷል፡፡

የሀገሪቱን ብሄራዊ አንድነትና ሉዐላዊነት በአስተማማኝ ሁኔታ ለመጠበቅ የሚችል ዘመናዊ መከላከያ የአየር ኃይልና የምድር ጦር፤ የፓሊስና የፌዋኖ ደራሽ ኃይል በጥራትና በብቃት በእውቀት ተገንብቷል፡፡ መከላከያ ኢንጂነሪግ በአገሪቱ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን የሲቪል፤ መካኒካልና ኤሌክትሪካል ኢንጂነሮችን አቅፎ የያዘ ነው፤ በአዳዲስ ፈጠራዎችና በምርምር ላይ በማተኮርም እየሰራ ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ በትራንስፎርሜሽን እቅዱ መሠረት በሦስት ዓመታት ውስጥ ታላላቅና እና ስኬታማ ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የበርካታ ዘመናዊ ቦይንግ

ጀቶች ባለቤትና በተደጋጋሚም ዓለም አቀፍ ተሸላሚ ለመሆን በቅቷል፡፡ የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ የአዳዲስ ትላልቅ የጭነት መርከቦች ባለቤት ሆኗል፡፡

የግል ተቋማት፣ ኮሌጆች፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ባንኮች፣ ኢንሹራንሶች፣ በአገሪቱ በስፋት ተከፍተው ውጤታማ ሥራ በመከወን ላይ ይገኛሉ፡፡ በመንገድ ትራንስፓርት ዘርፍ አገልግሎት ውስጥ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የግል ባለሀብቶች በህዝብ ማመላለሻ፣ በጭነትና በግንባታ ዘርፍ ተሰማርተው እየሰሩ ይገኛሉ፡፡

ኢትዮጵያውያን ኢንቨስተሮች ቀላልና ከባድ ፋብሪካዎችን ከፍተው የሥራ እድልም ለዜጎች ፈጥረው እየሰሩ ነው፤ የውጭ ኢንቨስተሮችም አገሪቱ ለኢንቨስትመንት ያላትን አመቺ ሁኔታ በመጠቀም በብዛት ገብተው ግንባታ አካሂደው በተለያዩ ዘርፎች በእርሻ፣ በጨርቃጨርቅ በኢንዱስትሪ፣ በከብት እርባታ፣ በማዕድን ፍለጋ ወዘተ ተሰማርተው አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ ኢትዮጵያ ያላት ሠላምና መረጋጋት ለውጭ ኢንቨስተሮች ተመራጭ አገር እንድትሆን አድርጓታል፡፡

ግልገል ጊቤ ሦስት ኃይል ማመንጫ ሥራው ተጠናቆ በቀጣዩ ዓመት ሥራውን ይጀምራል፡፡ ይህም የኤሌክትሪክ ኃይልን ለጎረቤት አገሮች ለመሸጥ ከመቻላችንም በላይ ለአገሪቱ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪን ያስገኛል፡፡

በሀገር ውስጥ ያለውን የስኳር ፍላጎት ሙሉ በሙሉ ከመሸፈንም አልፎ ወደ ውጭ በመላክ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት የሚችሉ በርካታ ግንባታዎች ያለማሰለስ ቀን ከሌሊት በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ እነዚህና ሌሎችም በኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽኑ መርሀ ግብር የተያዙ እቅዶች በታቀደላቸው ጊዜ ውስጥ ተሳክተዋል፡፡

ቀሪዎቹም እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡ በዚህ የተግባር ሂደት ፈተናና ውጣ ውረድ ውስጥ አመራሩም ሆነ ባለሙያው ለአገር እድገት የሚበጁ ሰፊ እውቀት ልምድና ተሞክሮ አግኝተዋል፡፡ ይህም ለቀጣይ አገራዊ የልማት ሥራዎች ከፍተኛ ዋጋ ያለው ግብዐት ሆኖ ያገለግላል፡፡ እስካሁን ባለፉት ሦስት ዓመታት ውስጥ የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን እቅዱ ከፍተኛ ድሎችን አስመዝግቧል፤ ቀሪዎቹም በስኬት ይጠናቀቃሉ፡፡